# የአየር ንብረት ለውጥና የአፍሪካ መጪው ተስፋ!

**ከሃብሮማይ**
ghabrom@yahoo.com

በዓለም አሁን አሁን የአየር ብክለት ችላ ብለን የማናልፍበት ደረጃ ላይ ደርሰናል፡፡በእያንዳንዱ እንቅስቃሴያችን የምናገኘው በጥቁር ጭስ የተሸፈነ አየር ነው፡፡ይህን ደግሞ ተፈጥሮ የሰጠችንን ንፁህ አየር እንዳንተነፍስና ትክክለኛውን የምድራችን ምቾት እንዳናገኝም እየገታንና ለተለያዩ ሕመሞችን እየዳረገን ይገኛል፡፡

የአየር ሙቀት መጨመር ከልብና ከመተንፈሻ አካላት ጋር ለተያያዙ በሽታዎች መንስኤ እንደሚሆን ሳይንሳዊ ግኝቶች ይጠቁማሉ፡፡ሳንባ ላይ በቀጥታ ከሚያደርሰው ጉዳት በተጨማሪ አስምን ለመሳሰሉ በሽታዎች መባባስ እንደ ምክንያት ይጠቀሳሉ፡፡

አሁን በዓለም ተፈጥሮ የሰጠችንን ንፁህ አየር ማግኘትና ማጣጣም ህልም እየሆነ መጥቷል፡፡

ከዚህ ቀደም ፖለተከኞችና ሳይንቲስቶች ስለ ዓለም ሙቀት ትኩረት እየሰጡ ለአከባቢ የሚስማማ የልማት ስትራተጂ ነድፈው የሚንቀሳቀሱበት አቅጣጫ አልነበረም፡፡

የአየር ንብረት ለውጥ የዓለምን ትኩረት ከመሳቡ በፊት አንዳንድ ሳይንቲስቶች የዓለም ሙቀት እየጨመረ መሆኑ አስገንዝበው ነበር፡፡ ምክንያቱም

የአየር ንብረቱ ከቀን ወደ ቀን ከዓመት ወደ ዓመት እየጨመረ ስለሆነ ትኩረት ብናደርግበት ብለው ሲማፀኑ ጆሮ የሚሰጣቸው ግን አላገኙም፡፡

ሳይንቲስቶቹ የመሬት ሙቀት ባለፉት መቶ ዓመታት የአንድ ዲግሪ ሴንቲግሬድ ጭማሪ አሳይቶ ነበር ፡፡ በሚመጡት መቶ ዓመታት ያደጉ አገሮች እንዲሁም በማደግ ላይ ያሉ አገሮች ለአከባቢ ትኩረት ሳይሰጡ በዚህ ከቀጠሉ የመሬት ሙቀት ወደ አስር ዲግሪ ሴንቲግሬድ ይደርሳል ብለው ገምቷል፡፡ ነገር ግን ለዚህ ትንበያ ትኩረት የሰጠው አልነበረም፡፡በቅርብ በወጣው ዘገባ የዓለም ሙቀት ከሁለት ዲግሪ ሰንቲግሬድ ወደ አራት ዲግሪ ሴንቲግሬድ እየጨመረ መሆኑን ተመልክተዋል፡፡

Intergovernmental Panel on Climate Change (IPCC) በ 2007 ባደረጉት ውይይት በሙቀት መጨመሩ ምክንያት በአንታርክቲክ የሚገኘው በረዶ በፍጥነት እንደሚቀልጥ፤ በውቅያኖሱ ላይ የሃያ ሰንቲሜትር ጭማሬ እንደሚያደርግና እኤአ በ 2100 ዓ.ም ባሕሩ ቢያንስ 30 ሰንቲሜትር ከፍተኛው ደግሞ 140 ሰንቲሜትር ይደርሳል ብለዋል፡፡

የበለፀጉት አገራት አሁን የደረሱበትን ደረጃ ላይ ለመድረስ አካባቢን ማእከል ባደረገ (Environment friendly development) ልማት ሳይሆን አካባቢን የሚበክል ልማት በመከተላቸው አሁን ያለንበት አሳሳቢ የአየር ብክለት ቀውስ ዳርገውናል፡፡

ያደጉት አገራት ይጠቀሙባቸው የነበሩና አሁን የሚጠቀሙባቸው ትላልቅ ኢንዱስትሪዎች ፤ የሃይል ማመንጫዎች፤ የነዳጅ ማጣሪያዎች ወዘተ በሙሉ አከባቢን የሚበክሉ ጋዞች ማለት ካርቦንዳይኦክሳይድ፤ ካርቦን ሞኖኦክሳይድ፤ ሃይድሮፍሎሮካርቦን፤ ሳልፈርዳይኦክሳይድና ናይትሮጅንዳይኦክሳይድ ወደ አየር የሚረጩ ናቸው፡፡

በአከባቢ (environment) የተለያዩ ጋዞች አሉ፡፡የሚቴን (methane) ና ካረቦንዳይኦክሳይድ ጋዞች በአየሩ እየጨመሩ በመምጣታቸው ምክንያት ግን በመጨረሻዎቹ ሁለት መቶ አምሳ ዓመታት የአየር ጋዞች እየተለወጡ መጥቷል፡፡ እነዚህ ጋዞች ከሌሎች ጋዞች ጋር ሲነፃፀሩ ሙቀት የመምጠጥ ዓቅማቸው ከፍተኛ ስለሆነ የፀሐይ ሙቀትን በአየሩ ውስጥ ያስገባሉ ነገር ግን ሙቀቱ ወደላይ እንዲወጣ አይፈቅዱም፡፡ስለሆነም አየሩ በጣም ሙቀታማ እንዲሆን ያደርጋሉ፡፡

ከላይ የጠቀስናቸው ጋዞች በአየር ላይ ሲቀላቀሉ አካባቢን የሚበክል ሁኔታዎች ይፈጠራሉ፡፡ለምሳሌ ሳልፈርዳይኦክሳይድና ናይትሮጅን ዳይኦክሳይድ በአየር ላይ ሲቀላቀሉ የአሲድ ዝናብ (acid rain) እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡ወደ መሬት ሲዘንብ በእርሻዎች፤በውሃ ለሚኖሩ እንስሳትና የተለያዩ መሰረተ ልማቶች ይጎዳል፡፡

በዚህ ምክንያትም በዓለማችን ያሉ እርሻዎች፤ ደኖች እንዲሁም በውሃ የሚኖሩ እንስሳቶች በአሲድ ዝናብ ክፉኛ ተጎድተዋል፡፡እየተጎዱም ናቸው፡፡ ደኖቹ እየተመናመኑ በመምጣታቸው ከተክሎቹ የምናገኘው ኦክስጅን በመቀነሱ ብክለቱን እንዲባባስ አድርጎታል ይላሉ በዘርፉ ጥልቅ ጥናት ያደረጉ ሳይንቲስቶች፡፡

ሌሎች የተለያዩ ጋዞች ወደ አየር በመቀላቀል የፀሐይ ጨረር የሚከላከልልን ኦዞን (ozone) የተባለ ሽፋን እያጠቁ ከፀሐይ ወደ መሬት የሚለቀቀውን ብርሃን የመቆጣጠር ዓቅሙ እየመነመነና የመሬትን ሙቀት አስፈሪ በሆነ ፍጥነት እየጨመረ መምጣቱን ይናገራሉ፡፡

ስለሆነም አሁን የዓለም ሙቀት በዓመት በ 2 ዲግሪ ሰንቲግሬድ (በ 3.6 ዲግሪፋሬንሀይት) ጨምሯል፡፡ይሄ የዓለም ሙቀት በፍጥነት መጨመር ደግሞ ለህዝቦቿ በጣም አሳሳቢና ትልቅ ስጋት ሆኖ ነው ያለው፡፡

አሁን ያለውን የዓለም የሙቀት መጠን መጨመር ዋነኛው ምክንያት ያደጉት አገሮች የተጠቀሙበት የኢነርጂ ፖሊሲ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡በኢነርጂ

ፖሊሲያቸው አከባቢን ማእከል ያደረገ አቅጣጫ ባለመከተላቸው የዓለም የአየር ንብረት ከፉኛ ተጎድተዋል፡፡በዚህ የተነሳም ይህ የሚባል ድርሻ የሌላቸው የአፍሪካ አገሮች ያደጉ አገሮች ባመጡት ጣጣ ተጠቂ ሆነዋል፡፡ ኢትዮጵያም ከአየር ሙቀቱ ተጠቂነት አላመለጠችም፡፡

ኢትዮጵያ ከቀረፀችው ፖሊሲና ስትራተጂ የኢነርጂ ፖሊሲ አንዱ ነው፡፡ፖሊሲው ስምንት ዋና ዋና ዓላማዎች አሉት፡፡ ከዓላማዎቹ መካከል ኢነርጂ በማመንጨትና በመጠቀም የሚመጣውን የአከባቢ ብክለት መከላከል የሚል ነው፡፡

ይህ የሚያሳየን አገራችን መላው ዓለም የአከባቢ ንብረት ለውጥ ትኩረት ስለሰጠች ያወጣችው ፖሊሲ ሳይሆን ከመጀመርያ ፖሊሲ ስትቀርፅና ወደ ልማት ስትነሳ አካባቢን ታሳቢ ያደረገ የልማት ስትራተጂ በመቀየሷ ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የአከባቢ ብክለት የሚያስከትሉ የሃይል ማመንጫዎች ለመከላከል በጥናት የተመሰረተ ቀጣይ ክትትል መደረግ እንደሚገባ አቅጣጫ አስቀምጣለች፡፡ ስለሆነም ኢንዱስትሪዎች የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ በካይ እንዳይሆኑና ከነሱ የሚወጡ ኬሚካሎች ወንዙንና አፈሩን እንዳይበክሉና ብሎም የህብረተሰቡ ጤና እንዳይጎዱ በካይ ነገሩን በሚገባ እንድይዙት ከሚካሉ ለሌሎች ግብአት ሊሆን የምችልበት አኳሃን እንዲፈጠር ትኩረት ተሰጥቶት እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው፡፡

ይህን የሕግ መሰረት እንዲኖረው የኢንዱስትሪ መከላከያ ደንብ ወጥቶለታል፡፡በሚኒስትሮች ምክር ቤትም ፀድቋል፡፡

ይህን የሚያሳየን የምናገኘው ዕድገት ልክ እንደበለፀጉ አገሮች በአንድ ጎኑ እየጠቀመን በሌላው አቅጣጫ ደግሞ ዋጋ እየከፈልን (opportunity cost) የሚሄድ ሳይሆን ፣ በሁሉም መልኩ ቀጣይነት ያለውና አስተማማኝ ዕድገት የሚያመጣና አከባቢን የማይበክል እንዲያውም የአከባቢ የአየር ንብረት የሚያሻሽል አቅጣጫ ነው ተከትሎ እየሄደ ያለው፡፡

በሃይል ምንጭ አቅርቦትን በተለይም የኤሌክትሪክ ሃይል አቅርቦት አገራችን የታደለች ነች፡፡ከ 30 ሺ ሜጋ ዋት በላይ የኤሌክትሪክ ሃይል ከውሃ ማመንጨት ትችላለች፡፡ ከፍተኛ ግምት ያለው ኤሌክትሪክ ከጅኦ ምንጭና ከነፋስም የማመንጨት ዓቅም አላት፡፡

ለወደፊቱ ከፀሃይ ብርሃን የኤሌክትሪክ ሃይልን በዋጋ ተወዳዳሪ በሆነ አኳሃን ማምረት የሚያስችል ቴክኖሎጂ ሲፈጠር ከፀሃይ ብርሃን ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ሃይል ለማመንጨት የሚያስችላት ዓቅም እንዳላትም ተረጋግጧል፡፡ ኢትዮጵያ ለራሷ የሚያሰፈልጋትን የኤለክትሪክ ሃይል አመንጭታ በተወዳዳሪ ዋጋና ጥራት በማቅረብ ምርቶቿ በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ የሚሆኑበትን ሁኔታ ከመፍጠር ባሻገር የኤሌክትሪክ ሃይሉን ወደ ውጭ አገር በመሸጥ ከፍተኛ ገቢ ማግኘት የምትችል አገር ነች፡፡

ኢትዮጵያ ያላትን የኤለክትሪክ ሃይል ምንጭ ታዳሽ (renewable) ና አካባቢን የማይበክል (environmental friendly) በመሆኑ ሃይል የማመንጨት ስራ አካባቢን እየበከለ ባለበትና መላው ዓለም አካባቢን ከሚበክል የሃይል ምንጭ ለመላቀቅ ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ባለበት በአሁኑ ወቅት አገራችን ከመጀመርያ ልዩ ግምት ሰጥታ እየተንቀሳቀሰች ነው፡፡

ኢትዮጵያ ኢነርጂ ስታመነጭ የአከባቢ ብክለት መቆጣጠር የሚል አቅጣጫ በፅሑፍ ብቻ ተፅፎ የቀረ ሳይሆን በተግባርም እየታየ ያለ ጉዳይ ነው፡፡

ለምሳሌ በሃይድሮኤሌክትሪክ የሚያመነጩ ያሉ ቦታዎች ማለት ቆቃ 43.2 ሜጋ ዋት፤ አዋሽ ሁለትና ሶስት 64 ሜጋ ዋት፤ ፊንጫ 134 ሜጋ ዋት፤ መልካ ዋኬና 153 ሜጋ ዋት፤ ጢስ አባይ አንድና ሁለት 84.4 ሜጋ ዋት፤ ግልገል ጊቤ አንድ 184 ሜጋ ዋት በጠቅላላ 669.9 ሜጋ ዋት የሚያመነጩት አከባቢን በመበከል ሳይሆን አከባቢው በሚስማማ መልኩ ነው፡፡

አሁን በኮንስትራክሽን ላይ ያሉ የሃይል ማመንጫዎች ግልገል ጊቤ ሁለት 420 ሜጋ ዋት፤ በለስ 460 ሜጋ ዋት ፤ ጊቤ ሶስት 1870 ሜጋ ዋት ግንባታውን አልቆ ወደ ሙከራ ተሸጋግሮ ያለውን የተከዜ የሃይል ማመንጫ 300 ሜጋ ዋት በሙሉ አከባቢን ማእከል ያደረገ እንጂ እንዳደጉት አገሮች አከባቢን የሚበክል አይደለም፡፡

ታዳሽ የኤለክትሪክ ሃይል ምንጭ በንፋስ እንዲሁም በጂኦተርማል የሚሰሩ የሃይል ማመንጫዎችም እንደዚሁ ለአከባቢ ተስማሚ ናቸው፡፡

በሌላም የኢትጵያ አየር መንገድ ስትራተጂውና ፖሊሲውን ለማሳካት አካባቢን የሚስማሙ አውሮፕላኖች በማስገባት ላይ ነው፡፡

በአገራችን የነበረው የደን ሽፋን ከፍተኛ ነው፡፡ በቅርቡ ግን የደን ሽፋናችን 3% ነበር፡፡ የዚህ ምክንያት ደግሞ የሕብረተሰቡ የደን ጭፍጨፋ እንዳለ ሆኖ የአየር ንብረት ለውጥ ያስከተለው ጫና ቀላል አይደለም፡፡ መንግስት ይህንን በመገንዘብ በ ሁለት ሺ ሁለት ዛፍ የሚል ፕሮግራም አውጥቶ ለሕብረተሰቡ ግንዛቤ በማሰጨበጥና በማሳተፍ ከ 700 ሚልዮን በላይ ችግኞችን ተተክለዋል፡፡

ሕብረተሰቡ ችግኞቹ ከመተከላቸው በፊት በቂ ግንዛቤ ስለጨበጠ አብዛኛዎቹ ችግኞች በመንከባከብ በጥሩ ደረጃ ላይ እንዲገኙ አድርጓቸዋል፡፡ ይህ ደግሞ የአየር ንብረቱ ቢያንስ ባለበት እንዲቆም የማይናቅ ድርሻ አለው፡፡

በሌላ በኩል ከነዳጅ ጋር እየተደባለቀ በአገልግሎት ላይ መዋል የጀመረውን የኤታኖል ምርት ትኩረት ተሰጥቶት በእንቅስቃሴ ላይ ነው፡፡

የስኳር ፋብሪካዎቻችን ስኳር ከማምረት በተጨማሪ ኤታኖልን እያመረቱ ነው፡፡ የፊንጫ ስኳር ፋብሪካ ከሌሎች የስኳር ፋብሪካዎች ለየት የሚያደርገው

የኤታኖል ፋብሪካ ስላለው ነው፡፡ፋብሪካውም አሁን ከሚያመርተው 8 ሚልዮን ሊትር ወደ 21 ሚልዮን ሊትር ኤታኖል ማምረት እንዲችል ጥረት እየተደረገ ነው፡፡

በተጨማሪ በመተሃራ ስኳር ፋብሪካ በቀን መቶ ሺ ሊትር ኤታኖል የሚያመርት የኤታኖል ፋብሪካ የሚገነባበት ጥናት ተካሂዷል፡፡የመጀመርያው ደረጃ የአጭር ጊዜ ዕቅድ በዓመት 13 ሚልዮን የማምረት ዓቅም ይኖረዋል፡፡

በአሁኑ ጊዜ በአዲስ አበባ ከነዳጅ ጋር እየተደባለቀ ያለው የኤታኖል ምርት በአስተማማኝ ደረጃ ጨምሮ ወደ ተለያዩ ከተሞቻችን እንዲስፋፋ እነዚህን ፋብሪካዎች ትልቅ አስተዋፆ አላቸው፡፡

እስካሁን በነዳጅ ላይ እየተደባለቀ ያለው ኤታኖል አምስት ፐርሰንት ብቻ ነው፡፡ እስከ አስር ፐርሰንት ኤታኖልን በነዳጅ መጨመር እንደሚቻል በጥናት እነደተረጋገጠ ለለሙያዎቹ ይናገራሉ፡፡ ሌሎች አገሮች የአከባቢያቸው አየር ንብረት መቆጣጠር ስለሚፈልጉ የኤታኖል ምርትን መፈለጋቸው የማይቀር ነው፡፡ ስለዚህ ከአገራችን በተጨማሪ ወደ ሌሎች አገሮችም ልከን የውጭ ምንዛሬ የምናገኝበት ዕድልም ይፈጥራል፡፡

የአገራችን ፖሊሲና ስትራተጂ ግብርና መር የኢንዱስትሪ ዕድገት (Agricultural Development Led Industrialization) በመሆኑ አብዛኛውን የሕብረተሰቡ ክፍል ማለት 84% በገጠር የሚኖር ስለሆነ የተለያዩ አትክልቶችና ሰብሎችን በመትከል የአገሪቷን የአየር ንብረት ለዜጎቿ ብቻ ሳይሆን ለጎረቤት አገሮችም ትልቅ አሰተዋፆ እንደምታደርግ አያጠያይቅም፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ አገራችን የአከባቢው አየር ንብረት ከብክለት ለመጠበቅና ከዚያም አልፎ አስተማማኝ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት እያደረች ናት፡፡

ያደጉ አገሮች አሁን ያላቸውን ደረጃ የደረሱት አካባቢን በመበከል ነው፡፡ እነሱ በኢኮኖሚ ህዝባቸውን ተጠቃሚ አድርገው የአየር ንብረቱን ለውጢል፡፡ አህጉራችን አፍሪካ ግን በኢኮኖሚም በአየር ንብረቱም ተጠቂ ሆናለች፡፡

በዚህ የዓለም አየር ብክለት ምንም አስተዋፆ ያልነበራት አህጉራችን አፍሪካ የአየር ንብረቱ ተጠቂ ሆናለች፡፡ ስለሆነም ባለፈው በአዲስ አበባ የተካሄድው የአፍሪካ ህብረት ስብሰባ ላይ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ አፍሪካ እጇ በሌለበት የአየር ንብረት ብክለት እየተቀጣች እንደሆነና በዚህ ምክንያትም በኢኮኖሚዋ ላይ ከፍተኛ ጫና እንዳደረሰባት በመጠቆም ያደጉት አገራት ለአህጉሪቷ ካሳ መክፈል እንዳለባቸው አስገንዝበው እንደነበር ይታወሳል፡፡

የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትለውን አደጋ ለመከላከል የዓለም መንግስታት በታህሳስ 2002 በዴንማርክ ርእሰ ከተማ ኮፐንሃገን የሚካሄደውን ጉባዔ አፍሪካ ወክለው እንዲደራደሩ ተመርጠዋል፡፡ ይህ የሆነው ምክንያት ኢትዮጵያ ከምታራመደው ያለች የኢነርጂ ፖሊሲና የምታመነጨው ያለችው ሃይል ከአከባቢ ተስማሚ በሆነ መልኩ ስለሆነ ነው፡፡

ሰሞኑም ጠቅላይ ሚኒስትሩ በኒውዮርክ ከተማ በአየር ንብረት ለውጥ ላይ የሚያየውን መድረክ እንዲመሩ ተመርጠዋል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ መድረኩን እንዲመሩ የተመረጡት በአከባቢ ጥበቃ ላይ ባላቸው ግንባር ቀደም ሚና መሆኑን በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በዓለም አቀፉ የአየር ንብረት ለውጥ በተለይም ከመጠን ባለፈ በሚለቀቀው በካይ ጋዝ ሰለባ የሆነችው አፍሪካ አደጋውን ለመከላከል የሚያስችላትን ስትራተጂ ቀርፃ አቋሟንም እየገለፀች ነው የምትገኘው፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በአየር ንብረት ለውጥ ውይይት ላይ በኒውዮርክ ስብሰባ እንዲመሩ መመረጣቸው በታህሳስ 2002 በዴንማርክ ኮፐንሃገን የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትለውን አደጋ ለመከላከል የዓለም መንግስታት

በሚያካሂዱት ጉባዔ ከተጨባጭ ውጤት ላይ ለመድረስ እንደሚያስችላቸው መገመት ይቻላል፡፡

አህጉራችን አፍሪካ ማግኘት ያለባትን ካሳ ከተሰጣት ኢኮኖሚዋ መንቀሳቀስ ባለበት አኳሃን የምታንቀሳቀስበት ዕድል ይፈጥርላታል ብየ አስባለሁ፡፡ ምክንያቱም የአህጉሪቷ ችግር ይተፈጥሮ ሃብተ ችግር ሳይሆን እሱን በተገቢው መንገድ ማንቀሳቀስ የሚያስችል ገንዘብ ነው፡፡ ስለሆነም ለአህጉራችን ህዝብ ብሩህ ተስፋ ቀላል የማይባል አስተዋፆ ይኖረዋል፡፡ሰላም!